DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ኮሮናቫይረስ 2019 (COVID-19)፣ የአገልግሎት እና ህክምና እንስሳት ለሚይዙ ሰዎች መመሪያ

## የምናዉቀው ነገር

- እስከ ዛሬ የሚገኘው ዉስን መረጃ ላይ በመመስረት፣ እንስሳት COVID-19ን ወደ ሰዎች የሚሰራጩበት አደጋ ዝቅተኛ እንደሆነ ተገምቷል።
- አሁንም ስለ ይህ ቫይረስ እየተማርን ነው፣ ነገር ግን አንድ አንድ ሁኔታዎች ዉስጥ ከሰዎች ወደ እንስሳት መሰራጨት የሚችል ይመስላል። በዓለም ዙሪያ ያሉ ትንሽ ቁጥር ያላቸው የቤት እንስሳት (ዉሾች እና ድመቶችን ጨምሮ) COVID-19 በሚያመጣ ቫይረስ፣ በብዛት COVID-19 ካለባቸው ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ከነበራቸው በኋላ፣ እንደተያዙ እና ከቫይረሱ እንዳገገሙ ሪፖርት ተደርጓል።
- በቫይረስ የተያዙ የቤት እንስሳት ሊታመሙ ወይም ምንም ምልክቶች ላይኖራቸው ይችላል። ከታመሙ የቤት እንስሳት ፣ብዙዎቹ መጠነኛ ህመም ብቻ ነበራቸው እና ሙሉ በሙሉ አገግሟል።

## ትርጓሜዎች

- **የአገልግሎት እንስሳት** እንደ ዉሾች ያሉ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ስራ ለመስራት ወይም ድርጊቶችን ለመፈፀም ለብቻ የሰለጠኑ ተብለው ይተረጉማሉ። በ አካል ጉዳተኛ የሆኑ አሜሪካኖች ሕግ መሰረት፣ የአገልግሎት እንስሳት ከያዥቸው ጋር እንዲቆዩ ሊፈቀድላቸው ይገባል። የአገልግሎት እንስሳትን የሚመለከት አካል ጉዳተኛ የሆኑ አሜሪካኖች ሕግ ድንጋጌዎች ላይ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ada.gov/service_animals_2010.htm ይመልከቱ።
- የ **ህክምና እንስሳ** በእንስሳ-የታገዘ ጣልቃ መግባት ወይም የህክምና ሂደት ዓይነት ዉስጥ ይጠቀማል።

## የአጠቃላይ መመሪያዎች

- የቤት እንስሳትን ከኢንፌክሽን ለመከላከል እርምጃ ይዉሰዱ። ለምሳሌ፣ ከቤተሰቡ ዉጭ ያሉ ሰዎች ወይም እንስሳት ጋር አላስፈላጊ ግንኙነትን ያስወግዱ። እንስሳን ለCOVID-19 ሊያጋልጥ የሚችልበት አካባቢ ሲወስዱት የእርስዎን የምርጥ ፍርድ ይጠቀሙ።
- በተቋማት ዉስጥ የህክምና እንስሳትን መጠቀም በአጠቃላይ ደህንነት ያለው ተደርጎ ተወስዷል፣ ይሁን እንጂ፣ የህክምና እንስሳትን በመደበኛነት የሚጠቀሙ የተናጥል ተቋማት በዚህ ጊዜ ሊፈቅዱ ወይም ላይፈቅዱ ይችላሉ።
- እርስዎ የአገልግሎት ወይም የህክምና እንስሳትን የሚይዙ ከሆነ፣ እና በ COVID-19 **ተመርምረው ፖዚቲቭ ከሆኑ**፣ለ COVID-19 ተመርምረው ፖዚቲቭ ለሆኑ ሰዎች የDC Health መመሪያን በ coronavirus.dc.gov/healthguidance ይመልከቱ።
- COVID-19 ያለበት ሰው ጋር ከተገናኘ በኋላ የእርስዎ **የአገልግሎት ወይም የህክምና እንስሳ ከታመመ** ፣ለእንስሳት ሀኪምዎ ይደዉሉ። እንስሳው COVID-19 ለሚያመጣ ቫይረስ ተመርምሮ ፖዚቲቭ ከሆነ፣ እንስሳዎ ተመርምሮ ፖዚቲቭ ሲሆን ምን እንደሚያደርጉ ምክረ-ሀሳቦችን በ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/daily-life-coping/positive-pet.htmlይከታተሉ።

## የአገልግሎት እንስሳትን የመጠበቅ መመሪያ

- የአገልግሎት እንስሳት እየሰሩ ሌሎች ሰዎች እና እንስሳት ጋር መሆን ሊኖርባቸው ይችላል። በተቻለ መጠን፣ ሁለቱም ያዥው እና እንስሳ ቢያንስ ከሌሎች ሰዎች እና እንስሳት 6 እግር ርቀ መቆየት አለባቸው።
- እንስሳው ከታመመ፣ ለእንስሳት ሀኪምን ይደዉሉ፣ እና ከእንስሳው ጋር ወደ ህዝብ የተሰበሰበበት ቦታዎች አይሂዱ።
- በተቻለ መጠን፣ ሰዎች በCOVID-19 የሚያዙበት መዋቅሮች ዉስጥ ወይም COVID-19 ሊኖራቸው የሚችሉ ሰዎች ጋር ግንኙነቶችን መከላከል የማይችሉበት ተቋም ዉስጥ የአገልግሎት እንስሳን ይዘው አይሂዱ።
- በተቻለ መጠን የታመሙ ሰዎች እና የአገልግሎት እንስሳ መካከል ግንኙነትን ያስወግዱ። ግንኙነቱ ሊወገድ የማይችል ከሆነ፣ የታመመው ሰው እንስሳ አካባቢ ሲሆን የፊት መሸፈኛ ጨርቅ መልበስ አለበት።
- የአገልግሎት እንስሳው የአንገት ጌጦች፣ አልባሳት ወይም መጋጠሚያዎች፣ እና ሌሎች አቅርቦቶችን በተደጋጋሚ ያጽዱ እና ዲስኢንፌክት ያድርጉ።

- በኬሚካል ዲስኢንፌክታንቶች፣ አልኮል፣ ሃይድሮጂን ፔሮክሳይድ፣ ወይም ለእንስሳ ጥቅም ያልፀደቁ ማንኛዉም ሌሎች ምርቶች የአገልግሎት እንስሳትን አይጥረጓቸው ወይም አያጥቧቸው። ቫይረሱ ከቤት እንስሳት ቆዳ፣የቆዳ ፀጉር፣ ወይም የራስ ፀጉር ወደ ሰዎች እንደሚሰራጭ የሚያሳይ ማስረጃ የለም።
- የፊት መሸፈኛዎችን የአገልግሎት እንስሳት ላይ አያስቀምጡ። የእንስሳን ፊትን መሸፈን ሊጎዳቸው ይችላል።

## የህክምና እንስሳትን የመጠበቅ መመሪያዎች

የህክምና እንስሳትን በመደበኛነት የሚጠቀሙ ተቋማት በዚህ ጊዜ ላይፈቅዱላቸው ይችላሉ ምክንያቱም በብዙ እነዚህ መዋቅሮች ዉስጥ ያሉ ሰዎች በ COVID-19 ምክንያት በከባድ ህመም ለመያዝ ከፍተኛ አደጋ ዉስጥ ናቸው። ለማህበራዊ ርቀት መጠበቅ፣ የፊት መሸፈኛዎች፣ እና COVID-19 እንዳይሰራጭ ለመከላከል የሚረዱ ሌሎች መንገዶች የDC Health መመሪያ እና የተቋም ፕሮቶኮሎችን ይከተሉ። **የህክምና እንስሳት ወደ ተቋም ወይም ሌላ መዋቅር እንዲመጡ ከተጋበዙ፣ ከዚህ በታች ያሉ ደረጃዎችን ይከተሉ።**

- የህክምና እንስሳ ጉብኝትቶች ደንበኞች እና የህክምን እንስሳት ቡድን መካከል የተወሰነ ደረጃ ንክኪን ይፈልጋል። በተቻለ መጠን፣ እንስሳትን ጉብኝቱ ዉስጥ ከሚሳተፉ ሰዎች እና እንስሳት ቢያንስ 6 እግር አርቀው ያቆዩአቸው። ያዦች እና ተሳታፊዎች በጉብኝቱ ጊዜ የፊት መሸፈኛ ጨርቅን መልበስ አለባቸው፣ ግለሰቡ በህክምና ሁኔታ ወይም አካልጉዳተኝነት ምክንያት የፊት መሸፈኛ ጭምብል መልበስ ካቃተው፣ ወይም የፊት መሸፈኛ ጭምብልን በአካል ማዉለቅ ካቃተው በስተቀረ።
- የህክምና እንስሳት ከታመሙ ወይም COVID-19 ለሚያመጣ ቫይረስ ተመርምረው ፖዚቲቭ ከሆኑ ወደ ጉብኝቶች ይዘዋቸው አይሂዱ።
- የ COVID-19 ምልክቶች ያሉባቸው ሰዎች የህክምና እንስሳትን መንካት፣ መቀራረብ፣ ወይም መገናኘት የለባቸውም። አንድ ሰው በ COVID-19 ከታመመ፣ ከህክምና እንስሳት ጋር ለመገናኘት እስከሚያገግሙ መጠበቅ አለባቸው።
- ከያንዳንዱ ግንኙነት በፊት እና በኋላ፣ ያዡው እና እንስሳውን የሚያንከባክብ ወይም ከእንስሳው ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛዉም ሰው እጃቸውን መታጠብ አለባቸው።
- በርካታ ሰዎች የሚይዙትን ቁሳቁሶች አይጠቀሙ፣ በተለይ ቁሳቁሶች በህክምና ጉብኝቶች መካከል ወደ በርካታ ተቋማት የሚወሰዱ ከሆነ (ለምሳሌ፣ መሳሪያዎች፣ መጋጠሚያዎች፣ መጫወቻዎች፣ ወይም ብርድ ልብሶች)። እንደ ህክምና መሳሪያዎች ያሉ ቁሳቁሶች ተቋማት መካከል መወሰድ ካለባቸው፣ ከያንዳንዱ መጠቀም ወይም ተቋም በኋላ ዲስኢንፌክት ያድርጉ።
- የእንስሳ አፍ ዉስጥ የሚገቡ እንደ መጫወቻዎች እና ማከሚያዎችን የመሰሉ ቁሳቁሶችን ሌሎች ሰዎች እንዲይይዙ አያደርጉ።
- መጫወቻዎች፣ የአንገት ጌጦች፣ መሳሪያዎች፣ መጋጠሚያዎች፣የህክምና አልባሳት እና ስካርቮች፣ እና የምግብ/ዉሃ ጎድጓዳ ሳህኖችን የመሰሉ ቁሳቁሶችን ዲስኢንፌክት ያድርጉ።
- የህክምና እንስሳት እንዲልሱ ወይም "እንዲስሙ" አይፍቀዱ።
- በኬሚካል ዲስኢንፌክታንቶች፣ አልኮል፣ ሃይድሮጂን ፔሮክሳይድ፣ ወይም ለእንስሳ ጥቅም ያልፀደቁ ማንኛዉም ሌሎች ምርቶች የህክምና እንስሳትን አይጥረጓቸው ወይም አያጥቧቸው። ቫይረሱ ከቤት እንስሳት ቆዳ፣የቆዳ ፀጉር፣ ወይም የራስ ፀጉር ወደ ሰዎች እንደሚሰራጭ የሚያሳይ ማስረጃ የለም።
- የፊት መሸፈኛዎችን የህክምና እንስሳት ላይ አያስቀምጡ። የእንስሳ ፊትን መሸፈን ሊጎዳው ይችላል።

## ተጨማሪ መጠቀሚያዎች

- በ COVID-19 ጊዜ የቤት እንስሳትን መጠበቅ ላይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ቀጥሎ ያለውን የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማእከላት (CDC) ድረገፅ፦ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/daily-life-coping/pets.html ይመልከቱ።
- ለተጨማሪ የ DC Health *መመሪያ፣ለቤት እንስሳ ባለቤቶች መመሪያ* እና *ስለ ቤት እንስሳት እና እንስሳት በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች* ጨምሮ፣ coronavirus.dc.gov/healthguidance ይመልከቱ።